በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

## የሐገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሐዋርያዊ ጉዞና ዘገባው።

**የሰማዕቷ የቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን በብፅ አቡነ ሕርያቆስ ተባርኮ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት ጀመረ**

በፈረንሣይ ክሌሞፎሩን በተባለው ከተማ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ኦርቶዶክሳውያን በቅድስት አርሴማ ማኅበር ስም ተሰባስበው በየወሩ የቅድስት አርሴማን ገድል አንብበው የወንጌል ትምህርት  መንፈሳዊ አገልግሎትን ያገኙ የነበር ቢሆንም ቅዳሴ የሚያገኙበት እድል አልነበረም ቤተክርስቲያን እንዲኖራቸው ቅዳሴ የሚቀደስበት ክርስትና የሚነሱበት ሥጋና ደሙ የሚፈተትበት  ቦታ ያስፈልገናል ብለው አስፈላጊውን ሁሉ በማሟላት (ንዋያተ ቅዱሳትን) እንዲሁም ቋሚ ቦታ(ቤተክርስቲያን) ከሚመለከተው አካል በማስፈቀድ ዝግጁ ሆነው ሲጠባባቁ ቆይተው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይህው ሐምሌ 14/2015 ዓ.ም (21/07/2023) ‹***ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንዳለ*** › መጽሐፋችን ጊዜው ሲደርስ በቅድስት አርሴማ ስም የተሰባሰቡት ምዕመናን ሥርዓተ ቤተክርስቲያን በጠበቀ መልኩ የሐገረ ስብከቱ ሥራስኪያጅ መልአከ ፀሐይ. አባ ገብረ ጻድቅ የተለያዩ የአድባራት አስተዳዳሪዎች ሊቃውንተ ቤተክርስያን በተገኙበት በብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ  ዓርብ ዕለት ከቀኑ ሰባት ላይ ቤተ መቅደሱ ተባርኮ አገልግሎቱ ጀምሯል።

ምዕመናን የነበራቸው ደስታ እና እንግዶችን ለመቀበል የሚያደርጉት ጥረት እጅግ የሚያስደምም ነበር ።የቤተክርስቲያን ልጆች ለቅዱሳን ያላቸው ፍቅር አጥንትን ሰርስሮ የሚገባ ነው በየሄዱበት በቅዱሳን በጻድቃን በሰማዕታት ስም በመሰባሰብ ሥርዓተ አምልኮታቸውን ይፈጽማሉ  ይህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መለያዋ እና መገለጫዋ ነው ።

ሌሊቱን በትምህርትና በማኅሌት ያደረ ሲሆን ቅዳሜ ጠዋት በብፁዕ አባታችን የተመራ ሥርዓተ ቅዳሴ ተከናውኖአል፣ በአካባቢው ያሉት ምዕመናን እና ከተለያየ አካባቢ የመጡ ክርስቲያኖች በሰማዕቷ ስም እዚህ ቦታ ላይ ቤተክርስቲያን መኖሩ ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማቸው ገልጸዋል። ከቅዳሴ ቦኃላ በነበረው ትምህርተ ወንጌል ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ ምስጋና አቅርበው አባታዊ ምክርና መንፈሳዊ ትምህርት አስተምረው መርሐግብሩ ተጠናቋል ።





**በተያያዘ ዜና ብፁዕ አባታችን እና የሐገረ ሥብከቱ ሥራ አስኪያጅ ቅዳሜ ዕለት የቅድስት አርሴማን በዓል አክብረው በቀጥታ ወደ ታላቁ ደብር ወደ ልዩን ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ ጉዞአቸውን ቀጥለዋል።**

## *ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ልዩን ፈረንሣይ*

## 15/10/2015   (22/07/2023)

ቅዳሜ ዋዜማ ፣ ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ የጣልያን  እና አካባቢው ሐገረ ስብከት ሊቀጳጳስ

መልአከ ፀሐይ አባ ገብረ ጻድቅ የጣልያን እና አካባቢው ሐገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ

የአድራባራት አስተዳዳሪዎች

ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን

ዲያቆናት (ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ )

መምህራን እና ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ምዕመናን በተገኙበት ዓመታዊው የሊቀ መልአኩን የቅዱስ ገብርኤልን በዓል ለማክበር ተሰባስበዋል ከዋዜማው ጀምሮ የነበረው መንፈስ እጅግ ነፍስን የሚመስጥ ፍጹም ያሬዳዊ አገልግሎት ነበር

*ዚቅ*

*ዘረዳእኮሙ ለሰማእት ወባላኃኮሙ እምእሳት*

*አድኃነነ እግዚኦ ሃሌ ሉያ እምዕለት እኪት ፡*

በደመቀና ሰማያዊ ደስታን ያጎናጽፍ የነበረው የሌሊቱ ምስጋና እንዳበቃ

በ16/10/2015 (23/07/2023) በብፁዕ አባታችን አቡነ ሕርያቆስ መሪነት ሥርዓተ ቅዳሴ ተከናውኖአል ። በቅዳሴው መሐል

***አንድ ዲያቆን ማዕረገ ቅስና ተሰጥቶታል***

***ሁሉት ታዳጊዎች ማዕረገ ዲቁና ተቀብለዋል***

ለእዚህ ለተሿሚዎቹ ስለ ክህነት አገልግሎትና ጥቅሙ ከእነርሱ ምን እንደሚጠበቅ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ትምህርትና ምክር ሰጥተዋል በብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ ተሰጥቶታል፥



***ከቅዳሴ ቦኃላ በነበረው መርሐ ግብር***

የልዮን ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልዕኮውን ለመወጣት ከሚያደርጋቸው ጥረቶች መካከል በተለያየ መልኩ ማደራጀት ፣ ማሰልጠን እና የአገልግሎት መድረኮችን ማመቻቸት ነው ለዚህ እንዲረዳቸው ለሰንበት ት/ቤት እና ለምዕመናን ሥልጠናዎችን በማድረግ ሠልጣኖቹን አስመርቀዋል ፣ ስለ ሥልጠናው ይዘት በፕሮጀክተር የተደገፈ አጭር ዳሰሳ ለብፁዕ አባታችን ገለጻ የተደረገላቸው ሲሆን ለሠልጣኖቹም የምስክር ወረቀት ከብፁዕ አቡነ ሕርያቆስና ከሐገረ ሥብከቱ ሥራ አስኪያጅ እጅ ተቀብለዋል ። በዚህ አጋጣሚም የደብሩ ሰበካ ጉባኤና የሰንበት ት/ቤት አባላት ለደብሩ አስተዳዳሪ ለመልአከ ሠላም ቀሲስ ሰሎሞን ኃይሌ ያላቸውን ፍቅርና የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጽ ሥጦታ በማዘጋጀት በብፁዕ አባታችን አማካኝነት አበርክተዋል በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ መንፈሳዊ ትምህርት ካስተማሩ ቦኃላ ታቦቱ ከመንበሩ ወርዶ ዑደት በማድረግ የሰንበት ት/ቤት መዘምራን አጅበውት ወደ መንበሩ ከተመለሰ ቦኃላ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል

በዚህ አጋጣሚ ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስና እና መልአከ ፀሐይ አባ ገብረ ጻድቅ (ሥራአስኪያጅ)

ሳምንቱን ሙሉ ያለ እረፍት ያደረጉትን ሐዋርያዊ ጉዞ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከእኛ ጋር በመሆን ያሳለፉትን ውጣውረድና ድካም የአባቶቻችን አምላክ ይቀበላቸው እንላለን